ሰኔ 1 ቀን 2008 ዓም
የኮ.መ.ቁጥር ------

ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት
14ኛ ወ/ችሎት
አዲስ አበባ

ከሣሽ፡- ፌደራል ዐቃቤ ሕግ
ተከሣሾች፡- ጌታቸው ሽፈራው አንዳርጌ

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 130 እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ች በመዝገብ ቁጥር 73514 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት የቀረቡ የክስ መቃወሚያዎች

1. ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ ተጥሷል በሚል የገለፀው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና ስለ ወንጀሉ የሰጠው ዝርዝር የማይጣጣም ስለመሆኑ፡-

ተከሣሽ የቀረበብኝ ክስ ግንቦት 7 ተብሎ የሚጠራው የሽብር ቡድን አመራሮች ጋር በፌስቡክና በስልክ ግንኙነት በመፍጠር የተለያዩ መረጃዎችን በማስተላለፍ የፀረ -ሽብር አዋጅን አንቀጽ 7/1 ተላልፈህ በሽብር ድርጅት ውስጥ በማናቸውም መልኩ የመሣተፍ ወንጀል ፈጽመሃል በሚል ነው ::

የተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌ መሠረት በሽብር ድርጅት ውስጥ መሣተፍ ከሚገለጽባቸው ሁኔታዎች አንዱ «በድርጅቱ በማናቸውም መልክ መሣተፍ » በሚል የተቀመጠ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ የሕጉ አነጋገር በማናቸውም ሁኔታ አንድ ሽብርተኛ ተብሎ የተሰየመን ድርጅት ስም መጥራት፣ የሽብር ድርጅቱ በሚጠቀምበት ሚዲያ መጠቀም ወይም የሽብር ድርጅቱ አባል ነው የተባለውን ሰው ለሽብር ድርጅቱ አንዳችም ፋይዳ በሌለው ነገር ላይ ማነጋገርን ሁሉ ይጨምራል በሚል ተለጥጦ ሊተረጎም አይገባም፡፡ በዚህ የአዋጁ ድንጋጌ በሽብር ድርጅት ውስጥ መሣተፍ ይገለፅባቸዋል በሚል ከተዘረዘሩት ተጨባጭ ሁኔታዎች(ሰው መመልመል፣ አባል መሆን እና ሥልጠና መውሰድ)አንፃር«በማናቸውም መልክ መሣተፍ»በሚል የተቀመጠው የሕጉ አነጋገር በጠባቡ ሊተረጎምና የሽብር ድርጅቱን ዓላማ በተጨባጭ ለማሣካት የሚችሉ ነገሮችን መፈፀም ወይም ማስፈፀምን ብቻ የሚመለከት ሆኖ የሚወስድ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አቃቤ ሕግ ተከሣሽ በተለያየ ጊዜ በአገሪቷ የተለያዩ ክፍሎች ስለነበሩ ክስተቶች ራሱ ዐቃቤ ሕግ የሽብር ቡድኑ

ዛ

ተቋማት መረጃ ማስተላለፍ በሕግ እንዳይደረግ የተከለከለ መሆኑን ወይም ተላለፈ የተባሉት መረጃዎች አሸባሪ ለተባለው የግንቦት 7 ድርጅት ዓላማ ማስፈፀሚያ የዋለ መሆኑን ዐቃቤ ሕግ በክሱ አልገለፀም ::ይልቁንም ተከሣሽ በሙያዮ ጋዜጠኛ እንደመሆኔ መረጃው ሌላ ወንጀል ለመፈፀም እንደሚያገለግል እያወቅሁኝ ሆነ ብዮ እስካላስተለፈኩኝ ድረስ ማንኛውንም መረጃ ተከታትዮ በማውጣት በሚዲያ አማካኝነት ለሕዝብ እንዲደርስ ማድረግ ሙያዮ የሚጠይቀኝ ግዴታዮ ነው እንጂ ወንጀል አይደለም:: በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ወንጀል ባልሆነ ጉዳይ እና ይልቁንም በጋዜጠኝነት ሙያዮ ያከናወንኳቸውን ተግባራት በመዘርዘር በዚህና በዚያ ቀን ለእከሌ እንዲህ ዓይነት መረጃ እንደሚያስተላልፍ ወይም እንዳስተላለፈ ገልፂል በሚል ያቀረበብኝ የወንጀል ክስ የሕጋዊነት መርህን በግልጽ የሚፃረር በመሆኑ የቀረበብኝ ክስ እንዲሰረዝልኝ አመለከታለሁ::

3. ተከሣሽ የተከሰስኩበትን ወንጀል ለይቼ አውቄ መልስ ለመስጠት እንድችል ግልጽ ሊሆኑ የሚገባውን ነጥቦች በተመለከተ የቀረበ መቃወሚያ (የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11/112)
    - 3.1. በክሱ የወንጀሉ ዝርዝር መግቢያ ላይ ተከሣሽ ከሽብር ቡድኑ ተልዕኮ እንደተቀበልኩኝ ከመባሉ ውጪ ተቀበልኩኝ የተባልኩት ተልዕኮ ምን እንደሆነ፣ መቼ፣ ከማን እና በምን ዓይነት መንገድ ተልዕኮውን እንደቀበልኩኝ ተለይቶ አልተገለፀም፣
    - 3.2. የሽብር ከሚጠቀምባቸው ሚዲያዎች ጋር የተለያዩ መረጃዎችን አስተለለፈ ከመባሉ በቀር በሽብር ቡድኑ የሚጠቀምባቸው ሚዲያዎች የትኞቹ እንደሆኑ እና የሽብር ቡድኑ የሚጠቀምባቸው ሚዲያዎች ማለትስ በሕግ ቋንቋን ምን ማለት እንደሆነ አልተገለፀም፣
    - 3.3. በክስ ዝርዝር ውስጥ አስተላለፍካቸው የተባልኳቸው መረጃዎች የሽብር ቡድን ለተባለው የግንቦት 7 ድረጅት ምን ጥቅም እንደሰጡ አልተገለፀም ፣
    - 3.4. በመዝገብ ቁጥር 112546 በሽብር ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ተብሏል ከተባለው አበበ ገላው ጋረ ግንኙነት አድርጓል ከመባሉ ውጪ ግንኙነቱን ያደረግሁት መቼ? የት ቦታእና በምን ዓይነት የመገናኛ ዘዴ እንደተገናኘሁ ያልተገለፀ ከመሆኑ በላይ ከዚሁ ግለሰብ ጋር በመሆን አደረግህ የተባልኩት የእመፅ ጥሪ መቼ ፣ የትና በምን ዓይነት መንገድ ጥሪውን እንዳቀረብኩኝ አልተገለፀም::

ሠ

በአጠቃላይ በዚህ በላይ በተገለፁት የከሱ ፍሬ ነገር ዙሪያ የተከሰስኩበትን ወንጀል ለይቼ እና አውቄ መልስ ለመስጠት እንድችል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 111 እና 112 በሚያዙት መሠረት የጊዜ ፤ የቦታ እና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎችን ዐቃቤ ሕግ አሟልቶ እንዲያቀርብ፤አማልቶ ማቅረብ የማይችል ከሆነ ደግሞ ክሱ ተሠርዞ በነፃ እንድሰናበት አመለከታለሁ፡፡

ተከሣሽ፡-

ጌራቸው ሽፈራው

አምኃ መኮንን
Ameha Mekonnen
በማናቸውም ፍ/ቤት ጠበቃና አማካሪ
Consultant & Attorney at Law